ታሪካዊ ዳራው

የትራምፕ አስተዳደር አንድ ሰው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ በሚጠይቅበት ጊዜ ለማመልከት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች ጋር በተያያዘ የመንግሥት መምሪያን ለመለወጥ እየሞከረ ይገኛል። እነዚህ መመዘኛዎች ሰውዬው “የማኅበራዊ ጥገኛ” እንዲሆን በማድረግ ይሆናል፣ ወይስ ወደፊት አንዳንድ ሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚጠቀም ይሆናል የሚለውን ለመለየት የተቀረጹ ናቸው።

በተለይም የቀረበው ሕገ መንግሥት እንደዚህ ሂደት አካል በማድረግ ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባው የሚችለው የፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞችን ዝርዝር ይገልጻል። የአንድ ሰው የአሁኑ ወይም ያለፈው ጊዜ የፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞች አጠቃቀም፣ ተቀባይነት ማግኘት ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘትን ሊያስከለክለው/ላት/ ይችላል።

Seattle
Office of Immigrant
and Refugee Affairs

ማስተባበያ፡-

ይህ FAQ ወይም “ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች” ሰነድ አጠቃላይ መረጃ ይይዛል፣ <u>ሕጋዊ ምክር አይደለም</u>። ስለ ተወሰኑ ሁኔታዎች ወይም የጥቅማ ጥቅሞችን መጠቀም ላይ ጥያቄዎች ካልዎት፣ ከስደተኞች ጠበቃ ወይም የBIA ዕውቅና ካለው ተወካይ ጋር መነጋገር አለብዎት።

1. “Public charge (ሕዝባዊ ክፍያ)” ምንድነው?

የፌዴራል መንግሥት “public charge (ሕዝባዊ ክፍያ)” የሚለውን ቃል የሚጠቀመው አንድ ስደተኛ ለመሰረታዊ ፍላጎቱ ወይም ፍላጎቷ ለማሟላት በዋናነት በመንግሥት ላይ ጥገኛ የሆነን ስደተኛ ለመግለጽ ነው። አዲስ በቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥር፣ መንግሥት ሕዝባዊ ክፍያን አንድ ሰው በህጉ ውስጥ የተዘረዘረውን የፌዴራል ሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞችን አንዱን ወይም ብዙውን የሚወስደው ሰው አድርጎ ለመግለጽ ይፈልጋል። (ስለእነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች የበለጠ ዝርዝር ለማግኘት ጥያቄ 4ን ይመልከቱ)

2. የሕዝባዊ ክፍያ ተጠቃሚ ከሆኑ የፌዴራል መንግሥት ይህን የሚለየው መቼ ነው?

የፌዴራል መንግሥት አንድ ሰው ወደ ዩናይት ስቴት ለመግባት በሚያመለክትበት ጊዜ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ (ሕጋዊ የሆነ ቋሚ መኖርያ ፈቃድ” የሚባለውን) ለማግኘት በሚያመለክትበት ጊዜ የሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻን ተግባራዊ ያደርጋል።

ለቪዛ ወይም ለመኖሪያ ፈቃድ በሚያመለክቱበት ጊዜ፣ የማመልከቻ ቅጽን ማስረከብ አለብዎት። ከቅጹ ላይ ወይም ከሚከተለው ቃለ መጠይቅ ላይ መረጃን መጠቀም፣ መንግሥት የ”ሕዝባዊ ክፍያ” ተጠቃሚ እንደሚሆኑ እና እንደማይሆኑ መንግሥት ይወስናል።

<u>ይህ የተወሰነው ፍተሻ የመኖሪያ ፈቃድ ከወሰደ በኋላ የዩናይት ስቴት ዜጋ ለመሆን በሚያመለክትበት ጊዜ ጥቅም ላይ አይውልም።</u>

3. የሕዝባዊ ክፍያ ተጠቃሚ ከሆኑ የፌዴራል መንግሥት ይህንን የሚወስነው እንዴት ነው?

በቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥር፣ የሕዝባዊ ክፍያ ውሳኔ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ መሰረት ያደርጋል። የስደተኞች ባለሥልጣን “totality of circumstances (ሙሉ በሙሉ ሁኔታዎቹን)”ፍተሻ ያደርጋል። ይህ ፍተሻ የአመልካቹን ዕድሜ፣ ጤና፣ የቤተሰብ ሁኔታን፣ ቋሚ ንብረት፣ ሀብቶቹን፣ የገንዘብ ሁኔታውን ይመረምራል። በሌላ አባባል፣ ወደፊት በሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ጥገኛ ስለመሆንዎ ለመወሰን መንግሥት በአጠቃላይ የእርስዎን የግል ሁኔታ መመልከት አለበት።

በተጨማሪም፣ በጹሑፍ የቀረበውን ድጋፍ በሕግ ግድ በሚሆንበት ጊዜ፣ እንደዚያ ዓይነት በጽሑፍ የቀረበ ግልጽ የሆነ ነገር በማይኖርበት ጊዜ ለሕዝባዊ ክፍያ መሰረት በሆኑ ነገሮች ላይ የሰውዬውን ተቀባይነት አለማግኘትን ይመሰርታል። በጽሑፍ የቀረበ ድጋፍ ኮንትራት የገባውን ሰው ማለትም “Sponsor (ስፖንሰር)” የተባለውን የገንዘብ ኃላፊነቱን ለሌላ ሰው ማለትም በቋሚነት ለመኖር ለሚመጣ ሰው እንዲፈርም በሕግ ያስገድደዋል።

4. በቀረበው አዲሱ ረቂቅ ሥር፣ ለሕዝባዊ ክፍያ ተቀባይነት ለማግኘት አዲሱ መመዘኛ ምንድ ነው?

በቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥር፣ ነገር ግን ባልጸደቀው ሥር፣ በአሁኑ ጊዜ ከሚከተሉት መርኃግብሮች ውስጥ የሚጠቀሙ ወይም ተጠቅመው ከሆነ ለሕዝባዊ ክፍያ

ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ። እነዚህ ቁርጠኝነቶች በተለያዩ ሁኔታዎች፣ ጊዜ እና የመጠቀሚያ ወቅቱን እና ጥቅማ ጥቅሞቹን የመውሰድ ዋጋን አካቶ፣ ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱንት ማለትም ጤና፣ ዕድሜ፣ እና የገንዘብ ምንጮች ላይ መሰረት ያደርጋል።

መርኃግብሮቹ ምልክት የሚደረግበት * አሁን ባለው የሕዝባዊ የክፍያ ፍተሻ ቅጽ ሥር ተቀባይነት ያገኛል። የቀረበው ረቂቅ ሕግ የቀሩትን መርኃግብሮችን ይጨምራል።

1. የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ መርኃግሮችን*፣ የሚያካትታቸው፡
   a. Temporary Assistance for Needy Families (TANF፣ጊዜያዊ ድጋፍ ለችግረኛ ቤተሰቦች)።*
   b. Supplemental Security Income (SSI፣የማሟያ የደህንነት ማስጠበቂያ ገቢ) ፣ ውስን የሆነ ገቢ ያላቸውን ሰዎች እና አካል ጉዳተኛ የሆኑትን፣ ዓይነ ስውር የሆኑትን ወይም 65 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑትን ሰዎች የሚያግዝ ነው።*
   c. General Assistance (አጠቃላይ ድጋፍ) ወይም ሌሎች የአከባቢ በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ የድጋፍ መርኃግብር።*
2. ለረጅም ጊዜ እንክብካቤ ተቋማዊ ማድረግ። *
3. Medicaid የጤና ወጪ ሽፋን፣ ድንገተኛ ከሆነ የጤና ሁኔታ እና አገልግሎት ውጪ ወይም ጥቅም ጥቅሞች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረገው በ Medicaid (ሜዲኬኤይድ) ሆኖ ነገር ግን በግለሰቦች ማለትም Individuals with Disabilities Education Act (IDEA፣ አካል ጉዳት ትምህርት አዋጅ) ሥር የሚሰጥ ሲሆን የዩናይትድ ስቴት ዜግነት ያላቸው ወላጆች በውጪ ለወለዳቸው ልጆች ጥቅማ ጥቅሞች ይሰጣሉ።
4. Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP፣ የምግብ ንጥረ ነገር ማሟያ ድጋፍ መርኃግብር)፣ ቀድሞ "የምግብ ማኅተሞች" ይባሉ ነበር።
5. Medicare Part D (ሜዲኬር ክፍል D) አነስተኛ ገቢ ላላቸው በሃኪም ለታዘዘ የመድኃኒት ወጪዎችን ይቀንስላቸዋል።
6. የፌዴራል የክራይ ድጋፍ፣ ማለትም Project Based Section 8 (ክፍል 8 የቤት ደረሰኞች) እና ማንኛውም የቤት ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው በ Project Based Section 8 (ፕሮጀክት መሰረት ያረገ ክፍል 8) ነው.
7. አንዳንድ ዋጋቸው የቀነሰ የቤት አገልግሎት በፌዴራል መንግሥት በኩል ይዘጋጃል።

5. በቀረበው አዲሱ ረቂቅ ሥር፣ ለሕዝባዊ ክፍያ ተቀባይነት ለማግኘት ከአዲሱ መመዘኛ ውስጥ የተቀነሱት መርኃግብሮች ምንድን ናቸው?

የአደጋ ጊዜ እርዳታ፣ የድንገተኛ የህክምና ድጋፍ ሰጪ፣ መንግሥት በመላው፣ አከባቢ፣ ወይም የጎሳ መርኃግብሮች (ከጥሬ ገንዘብ ሌላ ድጋፍ)፤ ጥቅማ ጥቅሞች በስደተኛው ቤተሰብ አባላት፣ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅማ ጥቅም በረቂቅ ሕጉ ላይ ያልተዘረዘረውን ይወስዳሉ። ያልተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቅሞች፣ ማለትም ትምህርት፣ የልጅ ዕድገት፣ እና ሥራ እና የሥራ ሥልጠና መርኃግብሮች በዚያ ውስጥ አይካተቱም። የፌዴራል መንግሥት Children's Health Insurance Program (CHIP፣ የልጆች የጤና መድኃን ዋስትና መርኃግብር) ላይ ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው በሚል የህዝብ አስተያየት ይፈልጋል።

ማንኛውም የ ስያትል ከተማ አካባቢ መርኃግብር ማለትም Utility Discount Program (የመጠቀሚያ ቅናሽ መርኃግብር) እና Seattle Preschool Program (የስያትል ቅድመ ትምህርት ቤት መርኃግብር) ተቀባይነት አይኖራቸውም።

በርካታ የስያትል (Seattle) መርኃግብሮችን በተመለከተ እርስዎ አግባቢነት ላሉበት፣ የራስዎ የስደተኛነት ሁኔታ ምንም ተፍእኖ ሳያደርግ ለማየት ወደሚቀጥለው ድኅረገጽ ይሂዱ: www.seattle.gov/affordable።

6. የቤተሰቤ አባላት የጤና እንክብካቤን፣ የተመጣጠነ ምግብን፣ ትምህርትን፣ ወይም ሌሎች መርኃግብሮችን ከተጠቀሙስ?

በአጠቃላይ፣ የፌዴራል መንግሥት እንደ አመልካች እርስዎን ብቻ የሚወስዱትን ጥቅማ ጥቅሞችን በቤተሰብዎ አባላት የሚወሰደውን ተቀባይነት እንዲኖረው አያደርግም። አዲሱ የቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥራ ላይ ከዋለ፣ የፌዴራል መንግሥት ልጆችዎ ጥሬ ገንዘብ ያልሆኑትን (ማለትም የጤና መድኅን ወይም የምግብ ማኅተም) ጥቅማ ጥቅሞን ለመኖሪያ ፈቃድ ወይም ዩናይትድ ስቴት ለመግባት ባቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት አያገኙም። ሆኖም ግን ያልዎት የልጆች ቁጥር፣ ዜጋ የሆኑ ልጆችን ላይ መሰረት ለማድረግ ለሕዝባዊ ክፍያ ውሳኔ አካል አድርጎ ሊቀበል ይችላል፤ ምክንያቱም የቤተሰብ መጠን ላይ ተፍእኖ ያደርጋል።

ስለ ራስዎ ጉዳይ ከስደተኞች ጉዳይ ጠበቃዎ ጋር እንዲነጋገር እንመክርዎታለን።

7. እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞችን ከዚህ በፊት ተጥቅመባቸው ከነበረ እና ከአሁን በኋላ ጥቅማ ጥቅሞቹን እየወሰድኩ ካልሆነስ?

የሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ ወደፊት ተግባራዊ ይደረጋል፤ ማለትም ፍተሻው ብቻውን ባለፈው ላይ ምን እንደተከሰተ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ከዚህ በፊት ጥቅማ ጥቅሞቹን ወስደው ከሆነ፣ ነገር ግን የእርስዎ ሁኔታ የተወለጠ ከሆነ፣ እነዚያን አገልግሎቶች አሁን እና ለወደፊትም (ለምሳሌ፡- አዲስ ሥራ ካለዎት) እንደማይፈልጉ ማመልከት ይችላሉ።

ስለ ተወሰኑ ሁኔታዎች ወይም የጥቅማ ጥቅሞችን መጠቀም ላይ ጥያቄዎች ካልዎት፣ ከስደተኞች ጠበቃ ወይም የBIA ዕውቅና ካለው ተወካይ ጋር መነጋገር አለብዎት።

8. ሕዝባዊ ክፍያ ለስደተኞቹ በሙሉ ተግባራዊ ይሆናል?

አይሆንም! ሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ሆነው ለዩናይትድ ስቴት ዜጋ ለመሆን ለሚያመለክቱ ተግባራዊ አይሆንም።

ደግሞም፣ አንዳንድ ሰብዓዊ የሆኑ ስደተኞች ለሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ ነጻ ይሆናሉ ወይም ለሕዝባዊ ክፍያ ጥቅማ ጥቅም ብቁ ይሆናሉ። ይህም የሚያካትተው፡

- መጠሊያ ጣቢያ ኗሪዎች
- መጠገቢያ ጥያቄዎች (ስደተኞች ሆነው ለጥገኝነት ያመለከቱ ወይም ያገኙ)
- ለመኖሪያ ፈቃድ ያመለከቱት በViolence Against Women Act (VAWA፣ በሴቶች ጥቃት አዋጅ ሥር ይሆናል)።
- U ቪዛ ወይም T ቪዛ ያላቸው ወይም ለዚያ ያመለከቱት
- Special Immigrant Juvenile Status (ልዩ የስደተኛ ወጣቶች ቪዛ) የሚፈልጉ ልጆች

ከእነዚህ ምድቦች በአንዱ ሥር እንኳን ከወደቁ፣ እርስዎ ተገቢነት ላልዎት ለየትኛውም ጥቅማ ጥቅሞች መጠቀም ይችላሉ። ይህም የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ፣ የጤና እንክብካቤ፣ የምግብ መርኃግብር፣ እና ሌሎች የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ያልሆኑ መርኃግብሮችን ያካትታል።

9. የመኖሪያ ፈቃድ ኖሮኝ አሁንም ጥቅማ ጥቅሞቹን እያገኘሁ ከሆነስ?

በቀረበው አዲሱ ረቂቅ ሕግ ሥር፣ እርስዎ፣ ልጅዎ፣ ወይም ሌሎች የቤተሰብዎ አባላት ሕጋዊ በሆነ መንገድ ጥቅማ ጥቅሞቹን ስለተጠቀሙ የመንሮያ ፈቃድዎን ሊነጥቁ ይችላሉ። ሕጋዊ በሆነ መንገድ ጥቅማ ጥቅሞቹን ስለተቀበሉ የዩናይትድ ስቴት ዜግነትን ሊከለከሉ አይችሉም።

10. የዩናይትድ ስቴት ዜግነት ኖሮኝ አሁንም ድረስ ጥቅማ ጥቅሞቹን እየወሰድኩ ከሆነስ?

ሕዝባዊ ክፍያ ለዩናይትድ ስቴት ዘጎችን ተግባራዊ አይደረጉም። የዩናይትድ ስቴት ዜጋ ሆነው ጥቅማ ጥቅሞቹን በመውሰድ ቀጥለው ከሆነ፣ ለእርስዎ ተገቢ የሆኑት ጥቅማ ጥቅሞችን ብቻ በመውሰድ መቀጠል ይችላሉ።

11. አሁን እየወሰድኩት ያለውን ጥቅማ ጥቅሞችን ማቆም አለብኝ?

ማቆም የለብዎትም! እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ወደ ሃኪም ጋር ለመሄድ፣ ምግብ ለመግዛት፣ ወይም ለቤት ኪራይ ለመክፈል ጥቅማ ጥቅሞችን እያገኙ ከሆነ፣ በቀረበው ረቂቅ ሕግ መሰረት በማድረግ የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞችን አያቋርጡ። የቀረበው ረቂቅ ህግ አስከ አሁን ተግባራዊ አልሆነም። ለወራት ያህል ሥራ ላይ አይውልም። የቀረበው ረቂቅ ሕግ ወደ ኃላ ተመልሶ ሥራ ላይ አይውልም፤ ይህም ማለት መንግሥት ሰውዬው የተጠቀመውን አዲስ የተጨመረውን ጥቅማ ጥቅሞች ሕጉ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ያለውን ቀናት አይመለከትም።

ሆኖም ግን፣ አስቀድሞ የነበሩት ጥቅማ ጥቅሞች የሕዝባዊ ክፍያ ውሳኔ ስለነበሩ፣ ማለትም TANF፣ SSI፣ እና የረጅም ጊዜ ተቋማዊ ማድረግ፣ መንግሥት ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ሊጠቀምባቸው ይችላል። የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ከስደተኞች ጠበቃ ጋር ይነጋገሩ።

12. የተዘረዘሩትን ጥቅማ ጥቅሞችን እያገኘሁ ከሆነስ?

በቀረበው ረቂቅ ሕግ ውስጥ የተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቅሞች ብቻ (ጥያቄ 4ን ይመልከቱ) ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል። ያልተዘረዘሩት ጥቅማ ጥቅሞች ማለትም ትምህርት፣ የልጅ ዕድገት፣ ነጻ እና ዋጋው ርካሽ የሆነ የትምህርት ቤት ምሳ፣ እና የሥራ እና የሥራ ሥልጠና መርኃግብሮች የሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ አካል አይደሉም።

ማንኛውም የአከባቢ ከተማ መርኃግብሮች ማለትም Utility Discount Program (የመጠቀሚያ እቃዎች መርኃግብር) እና Seattle Preschool Program (የስያትል የቅድመ መርኃግብር) ተቀባይነት የለውም።

በርካታ የስያትል (Seattle) መርኃግብሮችን በተመለከተ እርስዎ አግባቢነት ላሉበት፣ የራስዎ የስደተኛነት ሁኔታ ምንም ተፍእኖ ሳያደርግ ለማየት ወደሚቀጥለው ድኅረገጽ ይሂዱ: www.seattle.gov/affordable።

13. እንደ ሕዝባዊ ክፍያ ተጠቃሚ ሆኜ ከአገር መባረር እችላለሁ?

በአሁኑ ሕግ ሥር፣ ዳር በወጡ በአንዳንድ ጉዳዮች፣ የሕዝባዊ ክፍያ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ከአገር መባረር ይችላል። እነዚህ ሕጎች ዕድላቸው በጣም ጠባብ እና ፈጽሞ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ይታሰባል። ይህ አዲሱ ረቂቅ ለመወገድ ወይም ከአገር ለመባረር የሚያበቁ መመዘኛዎችን የሚተረጉም ወይም የሚያብራራ አይደለም።

14. በአዲሱ ረቂቅ ንድፍ ውስጥ ሌሎች የቀረቡ የትራምፕ ለውጦች ምንድ ናቸው?

በጥያቄ 4 ላይ የተዘረዘረው አዲስ መመዘኛ ጎን ለጎን፣ አዲሱ ረቂቅ ሀሳብ ሊሆን የሚችለው፡

ተመሳሳይ ፍተሻዎን ተግባራዊ የሚደረግባቸው፡

1) ለስደተኞች ያልሆኑ ቪዛን ለማራዘም ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡- በጉብኝት ቪዛዎ በመጠቀም በዩናይት ስቴት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ለመቆየት)፣ እና
2) ለስደተኞች ያልሆነ ሁኔታዎን ለመቀየር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡- ለተማሪ ቪዛ ወደ ሥራ ቪዛ ለመለወጥ)።

ስደተኛውም የኑሮውን ሁኔታ ለማስተካከል በሚፈልግበት ጊዜ ህጋዊ ስምምነት ማስገባት የሚያስፈልግበት ጊዜን ለመግለጽ። በቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥር፣ ለሕዝባዊ ክፍያ ተቀባይነት ያላገኘ ስደተኛ የሆነ ሰው ቢያንስ እስከ $10,000 ድረስ ለሕዝባዊ ክፍያ የጽሑፍ ስምምነት ማገባት ይችላል።

15. የጤና ሽፋን ጥቅማ ጥቅም ያገኙ የነበሩት ልጆችስ?

ለመኖሪያ ፈቃድ የሚያመለክቱ ልጆች ለቀረበው ረቂቅ አዲስ ሕጎች ሥር የሚታይ ሊሆን ይችላል። Medicaid እየወሰዱ ከሆነ፣ ዕድሜያቸውን፣ ገቢያቸውን፣ እና ሌሎች ሁኔታዎችን አካቶ ለሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ ሚዛን እንዲደፋ ሊያደርግ ይችላል። መንግሥት በመጨረሻው የህግ ለውጥ ውስጥ Children's Health Insurance Program (CHIP፣ የልጆችን የጤና መድኅን ዋስትናን መርኃግብርን) ለማካተት ወይም ላለማካተት ግብዓት ጠይቋል፤ ነገር ግን ይህ መርኃግብር በአሁኑ የቁጥጥር ጽሑፍ ውስጥ አልተካተተም። የዩናይትድ ስቴትስ ዜጎች የሆኑ ልጆች ለሕዝብ ድጋፍ ፍተሻ ተገዥ አይሆኑም።

16. አዲሱ የረቂቅ ሕግ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ግለሰቦች ላይ እንዴት ተጽእኖ ያደርጋል።

በአዲሱ ረቂቅ ሕግ ሥር፣ የሰውዬው ጤና በሕዝባዊ ክፍያ ውስጥ በመያዝ እና ባለመያዝ ላይ ለመወሰን መንግሥት ከሚያያቸው በርካታ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው። ይህም አካላዊ ወይም የአእምሮ የጤና ሁኔታዎች ማለትም የሰውዬውን የመስራት፣ ትምህርት ቤት የመማር፣ ወይም ለራሷ እንክብካቤ ለማድረግ እንዲያዳግታት የሚያደርጉን ያካትታል።

ሆኖም ግን፣ የቀረበው ረቂቅ ሕግ ለውጦች ሕጉ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ይወስዱት የነበሩት ጥቅማ ጥቅሞች (ሌሎች ከጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ውጪ ወይም የረጅም ጊዜ እንክብካቤ) ላይ ተግባራዊ እንደማይተገበሩ ይገጻል።

ስለ ራስዎ ጉዳይ ከስደተኞች ጉዳይ ጠበቃዎ ጋር እንዲነጋገር እንመክርዎታለን።

17. የመኖሪያ ፈቃድ አለኝ ነገር ግን ላድሰው እፈልጋለሁ። መንግሥት የእድሳት ማመልከቻዬን Medicaid ፣ የምግብ ማኅተሞችን፣ እና/ወይም የቤት ድጋፍን እየወሰድኩ ስለሆነ ሊከለከለኝ ይችላል?

አይከለከልም። የሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ የመኖሪያ ፈቃድን ሲያዲሱ ተግባራዊ አይሆንም። የእድሳት ማመልከቻ እርስዎ ብቁ ለሆኑበት መርኃግብርን መጠቀም ላይ መሰረት በማድረግ ሊከለከል አይችልም።

18. በተፈጥሮ የዩናይት ስቴት ዜጎች የሆኑት መርኃግሮቹን ማለትም Medicaid ወይምSNAP/የምግብ ኩፖኖች ከተጠቀሙ ዜግነታቸውን ያጣሉ?

አይሆንም! የዩናይትድ ስቴት ዜጎች ሕጋዊ የሆኑ የሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ስለተጠቀሙ ከዜግነታቸው ሊሰረዙ አይችሉም።

19. አዲሱ ረቂቅ የሚጸድቀው እና ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው መቼ ነው?

በእርግጠኝነት አናውቀውም። የፌዴራል መንግሥት የቀረበው ረቂቅ ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ እና ከመስራቱ በፊት፣ የ60 ቀናት የሕዝብ አስተያየት መስጫን ቀናትን አካቶ፣ ረጅም ሂደትን መከተል አለበት። መምሪያው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት፣ መንግሥት ማድረግ የሚገባው፡ ሕዝቡ ሀሳቡን እንዲሰጥ ዕድል መስጠት፣ እናለተቀበላቸው አስተያየቶችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እና መላሽ መስጠት።

20. ስለዚህ ፖሊሲ ምን እንደሚያስቡ ለፌዴራል መንግሥት መንገር ይችላሉ፡

የዚህ ረቂቅ ሕግ ገና አልጸደቀም። እንደ "የሕዝብ አስተያየት" በማድረግ የራስዎን ግብዓት በ"Federal Register (ፌዴራል መዝግብ)" ላይ በማቅረብ ስለ አዲሱ ረቂቅ ህግ የራስዎን ሀሳብ እስከ ሰኞ፣ ዲሴምቤር 10 ድረስ ማቅረብ አለብዎት። አስተያየቶችን በእንግሊዝኛ ብቻ መሰጠት ይችላሉ። አስተያየት ለማቅረብ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆን አይጠበቅብዎትም። የቀረበው ረቂቅ ሕገ መንግሥት ሁሉንም አስተያየቶችን ግንዛቤ ውስጥ እስከሚያስገባ ድረስ ተግባራዊ አይደረግም።

የስያትል (Seattle) ከተማ ከዚህ ከቀረበው ረቂቅ ሕግ ጋር የሚቃረን ሲሆን የሕዝብ አተያየትን ያቀርባል። የራስዎን ሀሳብ ለማቅረብ፣ እዚህ ጋር ይጫኑ፡- www.citiesforaction.us/publiccharge።